በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ
እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 21-31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም 1-10፤ 11-20 ጃንዋሪ 2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ - 3 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 4 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 5 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 5 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 5 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 7 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 7 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 8 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 8 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የቀኑ ዝነቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሽየስ በሚ.ሜ - 8 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 9 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

በዲሴምበር የሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዴት 3.2፤ በአዲግራት 4፣ 4፣ 4፣ 3.5፤ በሐሮማያ 0.2፣ 2 .2፣ 3.8፣ 4.8፣ 4.4፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.0፣ 2.8፣ 4.2፤ በአለም ከተማ 3.0፣ 4.2፣ 3.2፤ በአምባማሪያም 4.5፣ 4.5፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፤ በአርሲ ሮቤ 3.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 3.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.0፤ በባቲ 4.0፣ 3.8፣ 4.2፤ በቡኢ 3.6፣ 3.6፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 1.0፣ 2.4፤ በኮምቦልቻ 3.2፤ በደብረብርሀን 2.4፣ 4.2፣ 2.2፣ -1.0፣ 4.0፣ -2.8፤ በዳንግላ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.0፤ በደባርቅ 4.6፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.5፤ ደብረ ወርቅ 4.2፣ 4.2፣ 4.2፤ በቢሾፍቱ 4.2፣ 4.2፣ 4.1፣ 2.0፣ 4.0፣ 2.0፤ በእነዋሪ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፤ በፍቼ 3.5፣ 3.5፣ 3.0፤ በጉንዶ መስቀል 4.8፣ 4.3፣ 4.4፤ በእምድብር 4.8፣ 3.8፣ 4.1፤ በጃራ 4.0፣ በጅግጅጋ 2.4፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.0፣ 3.2፣ 4.0፣ 0.2፣ 1.0፣፤ በጅማ 4.8፣ 3.2፣ 1.4፤በማይጨዉ 4.5፣ 4.0፤ 4.8፣ 3.5፤ በመሐል ሜዳ 4.8፣ 3.0፣ 2.6፣ 4.5፣ 0.5፣ 1.2፣ -2.0፤ በሮቤ 3.8፣ 4.4፤ በሾላ ገቢያ 2.0፣ 1.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 3.3፣ 3.0. 2.1፣ 2.0፣ 1.1፤ በወገል ጤና 4.5፣ 4.2፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 0.6፣ 0.4፤ እንዲሁም በወረይሉ 4.5፣ 4.2 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጀመሪያዎቹ ሰባት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ከቀላል እሰከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በማሻ 64.2፣ 50.4፤ በሮቤ 36፤ በጅንካ 26.2፣ በሳዉላ 22.6፣ 7.5፤ በሰመራ 20.2፣ በጎሬ 15.5፤ በጋቲራ 13.8፣ 11.4፤ በተርጫ 8.0፣ በጭራ 7.4፣ እንዲሁም በፉጉዶ 5.2፣ 7.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በማሻ፣ በሮቤ፣ በሳዉላ በጅንካ፣ በጋቲራ፣ በሰመራ፣ በጎሬ በፉኙዶ እንዲሁም በጭራ ላይ እስከ 11 እስከ 119.4 ሚሜ የሚደርስ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሁሉም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከምዕራብ ኦሮሚያ ምስራቅ ወለጋ፤ ቡኖ በደሌ፣ ኢሊባቦር፣ ጅማ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፤ ከአፋር ክልል አዉሲ ዞን ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በተለይም በአስሩ ቀናቶች ላይ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በአንጻራዊ ሁኔታ ጠንከር ያለ ቅዝቃዜ ተስተዉሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በተወሰነ መጠን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በደቡብ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ጥቂት አካባቢዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል አስተዋጽኦ ነበረው ( ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ዲሰምበር ሶስተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ያመዘነ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂት የተፋሰስ ኪስ ቦታዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛዉ ባሮ አኮቦ እና በጥቂት በላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ አጋማሽ ቦታዎች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ መጠን ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው አዋሽ፣ አባይ፣ አፋር ደናክል፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ተከዜ፣ መረብ ጋሽ፣ አይሻ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ ተጽዕኖ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 5)፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ አሥር ቀናት በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡ በሌላ በኩል ከሚቀጥለው ሳምንት በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል (ካርታ 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የቀኑ ዝነቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሽየስ በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥለዉ የጃንዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የበጋው ደረቅ፤ ፀሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ለድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት የሚኖረውን ምቹ የአየር ሁኔታ በመረዳት ሰብልን ከማሳ የማንሳትና የማከማቸት እንዲሁም የመውቃት ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ከሳምንቱ አጋማሽ በኋላ በጥቂት ኪስ የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ  መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ  ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች መጠነኛ የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል አዎንታዊ ሚና ሊኖረው የሚችል ሲሆን በሌላ በኩልም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ከማዘጋጀት አንጻር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ጃንዋሪ አስር ቀናት ሁሉም የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር የሚቆዩ ሲሆን ይህም ሁኔታ በተለይም ከሚኖረው የቀኑ ትነት ጋር ተዳምሮ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ የውሃ ማጠራቀምያዎች ማለትም በግድቦች፣ በወንዞች፣ በኩራዎች እና በምንጮች ላይ መጠነኛ የውኃ መጠን መቀነስ ሊያስከትል ስለሚችል የሚገኘውን የውኃ ሀብት በአግባቡ እና ለብክነት በማያጋልጥ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et